# እ.ኤ.አ በኦክቶበር ወር 2023 በሲያትል የቤቶች ባለስልጣን( SHA) ላይ በተከሰተው የውሂብ ጥሰት የግል መረጃዎ ከተበረበረ እና/ ወይም ከተወሰደ ተመሳሳይ የይገባኛል ጥያቄ ካላቸው የግለሰቦች ቡድን ጋር በመሆን ከተከሳሹ በድርድር የእልባት መስጫ ስምምነት ክፍያ የማግኘት መብት ሊኖርዎት ይችላል።

ፍርድ ቤት ይህንን ማስታወቂያ አፅድቋል። ይህ በጠበቃ የሚቀርብ ጥያቄ አይደለም።

**ይህ ማስታወቂያ በመብቶችዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። እባክዎን በጥንቃቄ ያንብቡት።**

- እ.ኤ.አ በኦክቶበር 2023 በሲያትል የመኖሪያ ቤቶች ባለስልጣን (“SHA” ወይም “ተከሳሽ”) ላይ በተሰነዘረው የሳይበር ጥቃት በሳይበር ጥቃት ፈፃሚ ወንጀለኞች የግለሰቦችን የግል መረጃን የያዙ የተወሰኑ ፋይሎች ከተበረበሩበት እና/ወይም ከተወሰዱበት ክስተት (“የውሂብ ጥሰት”) ጋር በተያያዘ በቀረበ የቡድን አቤቱታ ክስ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ሳይሄድ ለማቋረጥ የእልባት መስጫ ክፍያ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ሀሳብ ቀርቧል። SHA የሚቀርቡበትን የይገባኛል ጥያቄዎች ሁሉ እንደማይቀበል እና የተሳሳተ ስራ እንደሰራ ወይም ተጠያቂ እንደሆነ ተደርጎ የሚነሱ ክሶችንም ሁሉ እንደማይቀበል አሳውቋል። የእልባት መስጫ ስምምነቱ ተከሳሹ የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን አምኖ መቀበሉን ወይም ተከሳሹ ማንኛውንም ሕግ መጣሱን የሚያመለክት ሳይሆን በተቃራኒው ክርክር በተነሳበት ጉዳይ ላይ የቀረቡ የይገባኛል ጥያቄዎችን እልባት ለመስጠት በስምምነት መፍታት ነው።
- የእልባት መስጫ ስምምነቱ ብቁ ለሆኑ ሰዎች የጥቅማጥቅም ክፍያዎችን ለማከናወን የሚያስችል የ $486,000.00 የካሳ ክፍያ ፈንድ/በጀት እንዲያዝ አስችሏል( ጥያቄ ከ 7-9 ን ይመልከቱ)። በተጨማሪም፣ የእልባት መስጫ ስምምነት ፈንድ የማስታወቂያ እና የይገባኛል ጥያቄ አስተዳደር ወጪዎችን፣ በፍርድ ቤት የተወሰኑ የጠበቃ ክፍያዎችን እና ወጪዎችን እንዲሁም ክስ አቅራቢ ቡድኑን ወክለው በችሎቱ ለነበሩ ሰዎች እንዲከፈል ፍርድ ቤቱ የወሰነውን የአገልግሎት ክፍያዎችን ይከፍላል።
- በክሱ ላይ ቢሳተፉም ባይሳተፉም ስምምነቱ በእርሶ ህጋዊ መብት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህን ማስታወቂያ በጥንቃቄ ያንብቡት። ለተሟላ ዝርዝር መረጃ፣ www.SeattleHADataIncident.com ይጎብኙ ወይም በነፃ የስልክ ጥሪ መስመር ቁጥር 1-844-405-6502 ላይ ይደውሉ።.

| በዚህ የእልባት መስጫ ስምምነት ውስጥ ያልዎት ህጋዊ መብቶች እና አማራጮች | |
|---|---|
| የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅፁን እ.ኤ.አ እስከ: ኖቬምበር 19, 2025 ድረስ ሞልተው ያስገቡ | ማናቸውንም የእልባት መስጫ ስምምነት ጥቅማጥቅሞችን የሚያገኙበት ብቸኛው መንገድ። |
| የስምምነቱ አካል መሆን የማይፈልጉ ከሆነ እ.ኤ.አ እስከ ኦክቶበር 20 ቀን፣ 2025 ድረስ ከጉዳዩ እራስዎን በማግለል | የጥቅማጥቅሞች ተጋሪ አይሁኑ። በዚህ የእልባት መስጫ ስምምነት ለተፈቱት የይገባኛል ጥያቄዎች በ SHA ላይ የራስዎን የግል ክስ በተናጠል የመመስረት መብትዎን ይጠብቁ። |
| እስከ ኦክቶበር 20 ቀን 2025 ድረስ በእልባት መስጫ ስምምነቱ ላይ ተቃዉሞ ማቅረብ ይችላሉ። | የእልባት መስጫ ስምምነቱ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ብለው የሚያምኑበትን ምክንያት ለፍርድ ቤቱ ያስረዱ። እንዲሁም እ.ኤ.አ **በ ዲሴምበር 5 ቀን 2025**,በሚካሄደው ችሎት ላይ ስለ እልባት መስጫ ስምምነቱ ፍትሃዊነት ከጠበቃዎ ጋር ወይም ለብቻዎ በችሎቱ ፊት በመቅረብ ለማስረዳት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። |
| እርምጃ ካልወሰዱ | ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ምንም ገንዘብ ወይም ጥቅማጥቅም አያገኙም ነገርግን አሁንም ለስምምነቱ ውሎች እና ቅድመ ሁኔታዎች ተገዢ ይሆናሉ። |

- እነዚህ መብቶች እና አማራጮች – እንዲሁም እነሱን ለመጠቀም የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች – በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ተብራርተዋል።
- ይህንን ጉዳይ እየተመለከተ ያለው ፍርድ ቤት አሁንም የእልባት መስጫ ስምምነቱን ማፅደቅ ወይም አለማፅደቁን መወሰን አለበት። ፍርድ ቤቱ ስምምነቱን ካፀደቀ እና ሁሉም የይግባኝ ጥያቄዎች ከተፈቱ በኋላ ጥቅማጥቅሞች የሚከፋፈሉ ይሆናል።

**ጥያቄዎች አልዎት? www.SeattleHADataIncident.com ይጐብኙ ወይም ከክፍያ ነፃ የጥሪ መስመር ቁጥር 1-844-405-6502 ላይ ይደውሉ።**

## ይህ ማስታወቂያ ምን ይይዛል


መሰረታዊ መረጃ ........ ገፅ 3

1. ይህ ማስታወቂያ ለምን ደረሰኝ?
2. ይህ ክስ ስለ ምንድነው?
3. የቡድን አቤቱታ ክስ ምንድነው?
4. ለምን የእልባት መስጫ ስምምነት ላይ ተደረሰ?

በእልባት መስጫ ስምምነቱ ውስጥ ማን ይካተታል? ........ ገፅ 3-4

5. የእልባት መስጫ ስምምነቱ አካል መሆኔን እንዴት አውቃለሁ?
6. ለመካተት መሟላት ያለባቸው ልዩ ሁኔታዎች አሉ?

ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ለሚገኙ ጥቅማ ጥቅሞች—እርስዎ ብቁ ከሆኑ ምን ያገኛሉ ........ ገፅ 4-5

7. የእልባት መስጫ ስምምነቱ ምን ያስገኛል?
8. ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ምን ማግኘት እችላለሁ?
9. የቡድኑ አካል ሆኜ መቆየቴ ምን ያሳጣኛል?

ጥቅማጥቅሞችን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል—የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ማስገባት ........ ገፅ 5

10. ክፍያ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?
11. የሚከፈለኝ ክፍያ ምን ያህል ይሆናል?
12. ክፍያዬን መቼ ነው የማገኘው?

እርስዎን የሚወክሉ ጠበቆች ........ ገፅ 5-6

13. በዚህ ጉዳይ ጥብቅና የሚቆምልኝ አለ?
14. የእራሴን ጠበቃ መያዝ እችላለሁ?
15. ለጠበቃው ክፍያ የሚከፈለው እንዴት ነው?

ከእልባት መስጫ ስምምነቱ እራስዎን ማግለል........ ገፅ 6-7

16. ከእልባት መስጫ ስምምነቱ እራሴን እንዴት ማግለል እችላለሁ?
17. የእልባት መስጫሽ ስምምነት ቡድኑ አባል ከሆንኩ እና እራሴን ከቡድኑ ካለገለልኩ በቀጣይ ይህን ጉዳይ አንስቼ በተከሳሽ ላይ ክስ መመስረት እችላለሁ?
18. እራሴን ከቡድኑ ለማግለል ከመረጥኩ ምን ይፈጠራል?

በእልባት መስጫ ስምምነቱ ላይ አስተያየት መስጠት ወይም ስምምነቱን መቃወም........ ገፅ 7

19. እልባት መስጫ ስምምነቱን እንዳልወደድኩት ለፍርድ ቤቱ እንዴት ማስረዳት እችላለሁ?
20. በመቃወም እና እራስን ከጉዳዩ በማግለል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ፍርድ ቤቱ የፍትሃዊነት ጉዳይን የሚመለከትበት የመጨረሻ ችሎት ........ ገፅ 8

21. ፍርድ ቤቱ ስምምነቱን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የሚወስነው መቼ እና የት ነው?
22. በፍትሃዊነት ላይ በሚካሄደው ችሎት ላይ መገኘት አለብኝን?
23. በችሎቱ ወቅት መናገር እችላለሁ?

ምንም እርምጃ ካል ወሰድኩ........ ገፅ 8

24. ምንም እርምጃ ካልወሰድኩ ምን ይፈጠራል?

ተጨማሪ መረጃ ስለማግኘት ........ ገፅ 8

25. ስለ ስምምነቱ ተጨማሪ ዝርዝሮች ማግኘት ይቻላል?
26. ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

## መሰረታዊ መረጃ

### 1. ማስታወቂያ የደረሰኝ ለምንድን ነው?

በፖስታ ካርድ ወይም በኢሜል ማስታወቂያ የደረስዎት በውሂብ ጥሰቱ ወቅት መረጃዎ የተበረበረ እና/ ወይም የተወሰደብዎ ሊሆን የሚችል ግለሰብ ሆነው በመለየትዎ ነው። በመረጃ ጥሰቱ ወቅት የግል መረጃዎቹ ተበርብረውብኛል እና/ወይም ተወስደውብኛል የሚሉ አንዳንድ ግለሰቦች በ SHA. ላይ የቡድን አቤቱታ ክስ አቅርበዋል። SHA የቀረበበትን ክስ አስተባብሏል እንዲሁም ክሱ ወደ ፍርድ ቤት ከሄደ ተጠያቂ እንደማይሆን አስታውቋል። ከሳሽ እና ተከሳሽ/ሁለቱም ወገኖች ጉዳዩን ለመፍታት በሚያስችል መንገድ ላይ እልባት በመስጠት መስማማት የሚያስችል ሀሳብ አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱ ማስታወቂያ እንዲላክ ያዘዘው በዚህ የቡድን አቤቱታ ክስ እልባት መስጫ ስምምነት ላይ መድረስ የሚያስችል ሀሳብ በመቅረቡ እና ፍርድ ቤቱ ይህን እልባት መስጫ ስምምነት ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ከመወሰኑ በፊት ስለሚኖሩት ሁሉም አማራጮችዎ የማወቅ መብት ስላልዎት ነው። ፍርድ ቤቱ እልባት መስጫ ስምምነቱን ካፀደቀው፣ተቃውሞዎች ወይም ይግባኞች ካሉ፣ መፍትሄ እንዲያገኙ ከተደረገ በኃላ፣ በፍርድ ቤቱ የሚሰየም የእልባት መስጫ ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪ በስምምነቱ የሚካተቱ ጥቅማጥቅሞችን ትክክለኛ የይገባኛል ጥያቄ ላቀረቡ፣ የአቤቱታ አቅራቢ ቡድን አባላት ያከፋፍላል እንዲሁም በ SHA ላይ የቀረቡ በእንጥልጥል ላይ ያሉ የይገባኛል ጥያቄዎች ተዘግተው ውድቅ ይደረጋሉ።

ይህ ማስታወቂያ የቀረበውን ክስ፣ የእልባት መስጫ ስምምነቱን፣ በሕግ የተፈቀደልዎት መብቶችን፣ ምን ጥቅማጥቅሞች እንደሚያገኙ፣ እነዚህን ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት ማን ብቁ እንደሆነ እና እንዴት ጥቅማጥቅሞቹን ማግኘት እንደሚችሉ ያብራራል። የክስ ጉዳዩ መጠሪያ *Lewis et al. v. Seattle Housing Authority*ሲሆን፣ የጉዳዩ ቁጥር. 24- 2-16171-6 SEA, ነው ጉዳዩ በአሁኑ ወቅት በዋሽንግተን ግዛት፣ በኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ በመታየት ላይ ይገኛል።

### 2. ክስ የቀረበበት ጉዳይ ምንድን ነው?

ከሳሾች SHA ለውሂብ ጥሰቱ ተጠያቂ እንደሆነ ገልፀዋል እንዲሁም በርካታ ሕጋዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን በ SHA ላይ አቅርበዋል። SHA በክሱ ላይ የተነሱ የይገባኛል ጥያቄዎችን እና ሙግቶችን ሁሉ ውድቅ አድርጓል።

### 3. የቡድን አቤቱታ ክስ ምንድነው?

በቡድን አቤቱታ ክስ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች "የቡድን ተወካዮች" በራሳቸው ስም እና ተመሳሳይ የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳሏቸው የሚያነሱ ሌሎች ሰዎችን በመወከል ክስ ያቀርባሉ። ይህ የሰዎች ቡድን "ቡድን" ተብሎ ይጠራል፣ በቡድኑ ውስጥ ያሉት ሰዎች ደግሞ "የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባላት" ወይም "የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን" ተብለው ይጠራሉ። እራሳቸውን ከእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ ለማግለል ከመረጡ ሰዎች በስተቀር፣ አንድ ፍርድ ቤት ሁሉንም የስምምነት ቡድን አባላት ጉዳዮች ይፈታል። በዚህ ጉዳይ ላይ ክስ ያቀረቡት—Lakisha Lewis እና Czarina Slape—ሲሆኑ ከሳሾች ተብለው ይጠራሉ። ክስ የቀረበበት አካል —SHA—ሲሆን ተከሳሽ ተብሎ ይጠራል።

### 4. ለምን እልባት መስጫ ስምምነት ላይ ተደረሰ?

ፍርድ ቤቱ ለከሳሾቹም ሆነ ለተከሳሹ የፍርድ ውሳኔ አልሰጠም። ይልቁንም ሁለቱም ወገኖች በጉዳዩ ላይ እልባት መስጫ ስምምነት ላይ ለመድረስ ተስማምተዋል። በዚህ መንገድ፣ ከፍርድ ቤት ሂደት ጋር የተያያዙ ወጪዎችን እና ስጋቶችን ያስወግዳሉ፣ እንዲሁም የቡድኑ አባላት ጥቅማጥቅሞችን ወይም ካሳዎችን ሊያገኙ ይችላሉ። የቡድኑ ተወካዮች እና የቡድኑ የህግ አማካሪዎች እልባት መስጫ ስምምነቱ ለቡድኑ የሚበጅ ነው ብለው ያምናሉ።

## በእልባት መስጫ ስምምነቱ ውስጥ ማን ይካተታል?

### 5. የእልባት መስጫ ስምምነቱ አካል እንደሆንኩ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

የእልባት መስጫ ስምምነቱ ቡድን ተብሎ የሚጠራው:"በመረጃ ጥሰቱ የግል መረጃዎቻቸው የተበረበሩባቸው እና/ወይም የተወሰዱባቸው" ሁሉም የአሜሪካ ነዋሪዎችን ያካትታል።. በግምት 72,000 የሚደርሱ የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባላት አሉ።

## 6. በእልባት መስጫ ስምምነቱ ውስጥ ለመካተት መሟላት ያለባቸው ልዩ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ?

አዎን፣ የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ በተለይ የሚከተሉትን አያካትትም:-( 1) በዚህ ክስ ላይ የተመደቡ ዳኞች እና የቤተሰቦቻቸው አባላት፤ (2) ተከሳሽ፣ ቅርንጫፍ ኩባንያዎቹ፣ እናት ኩባንያዎች፣ ቀጣይ ተተኪ ኩባንያዎችን፣ ቀዳሚ ኩባንያዎችን፣ እናተከሳሽ ወይም እናት ኩባንያዎቹ የሚቆጣጠሩት ማናቸውም አካላትን እንዲሁም የኩባንያው የአሁን ወይም የቀድሞ ሰራተኞችን እና ዳይሬክተሮችን፤ እና (3) እራስን ከጉዳዩ ለማግለያ የተሰጠው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ሕጋዊ የሆነ እራስን የማግለል ጥያቄ የሚያቀርቡ የስምምነት ቡድን አባላትን።

## የእልባት መስጫ ስምምነቱ ጥቅማጥቅሞች—ብቁ ከሆኑ የሚያገኙት

## 7. እልባት መስጫ ስምምነቱ ምን ያስገኛል?

በእልባት መስጫ ስምምነቱ መሠረት SHA ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ጋር የተገናኙ ጥቅማጥቅሞች እና ተዛማጅ ወጪዎች ለመክፈል $486,000 ልዩ ፈንድ/በጀት የሚይዝ ሲሆን ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ ሁሉም ክፍያዎች እና ወጪዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ወደ ተከሳሹ ይመለሳል። ይህ ገንዘብ እልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባላት ያቀረቡት ሁሉንም ትክክለኛ የሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎች፣ የማስታወቂያ እና የአስተዳደር ወጪዎችን፣ የአገልግሎት ክፍያዎችን እና የጥብቅና ክፍያዎችን እንዲሁም ወጪዎች ለመክፈል ያገለግላል። በምንም አይነት ሁኔታ SHA ከ $486,000.00 በላይ አይከፍልም።

## 8. ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ምን ማግኘት እችላለሁ?

የስምምነቱ ቡድን አባላት ከሚከተሉት የገንዘብ ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ለማግኘት የሚያስችል የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

- **ከኪስ ውጭ በተደረገ ገንዘብ ሳቢያ ለተከሰቱ ኪሣራዎች ተመላሽ ገንዘብ ማግኘት:-** ሁሉም የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባላት ከኪሳቸው ውጭ ባደረጉት ገንዘብ ሳቢያ ለተከሰቱ በሰነድ የተደገፉ ኪሣራዎች እስከ አምስት ሺህ ዶላር እና ዜሮ ሳንቲም ($5,000.00). ድረስ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ከኪስ ውጭ በተደረገ ገንዘብ ሳቢያ የተከሰቱ ኪሣራዎች ማለት ከተከሰተው የውሂብ ጥሰት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ እና አንድ ተሳታፊ የስምምነት ቡድን አባል ከፍሏቸው ተመላሽ ያልተደረጉ ወጪዎች ወይም ክፍያዎች ሲሆኑ፤ እነዚህም የሚከተሉትን የሚያካትቱ ሲሆን ነገርግን በእነዚህ ብቻ የተገደቡ አይደሉም።: (i) ከማጭበርበር ወይም ከማንነት ስርቆት ጋር የተያያዙ ተመላሽ ያልተደረጉ የገንዘብ ኪሣራዎች፤ (ii) የጠበቃ ክፍያዎችን፣ የሒሳብ ባለሙያ ክፍያዎችን እና ለክሬዲት ጥገና አገልግሎት የሚከፈል ክፍያን የሚያካትት የባለሙያ ክፍያዎች፤ (iii) እ.ኤ.አ ከኦገስት 9, 2023 በኋላ በማንኛውም የክሬዲት ሪፖርት አድራጊ ኤጀንሲ አማካኝነት በክሬዲት ላይ እገዳ ከመጣል (freezing) ወይም ከማንሳት (unfreezing) ጋር የተያያዙ ወጪዎች፤ (iv) እ.ኤ.አ በኦገስት 9 ቀን 2023 እና ከዚያ በኋላ ካሉ ቀናት አንስቶ የይገባኛል ጥያቄ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ባሉ ቀናት የተከሰቱ የክሬዲት ክትትል ወጪዎች; እና (v) እንደ ኖተሪ፣ ፋክስ፣ ፖስታ፣ ኮፒ፣ በመኪና ለተሸፈነ የጉዞ እርቀት የወጣ ወጪ እንዲሁም የረጅም ርቀት የስልክ ጥሪ ክፍያዎች ያሉ ልዩ ልዩ ወጪዎች። ከኪስ ውጭ በተደረገ ገንዘብ ሳቢያ የተከሰቱ ኪሣራዎች ያጋጠማቸው ተሳታፊ የስምምነት ቡድን አባላት የሚያቀርቡትን የይገባኛል ጥያቄን ለመገምገም የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሚከተሉትን ጨምሮ ለስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው ማቅረብ አለባቸው:-( 1) ተሳታፊ የስምምነት ቡድኑ አባል ስም እና ወቅታዊ መገኛ አድራሻ፤ (2) የይገባኛል ጥያቄያቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃ ሰነዶች፤ (3) የኪሣራው ባህሪ ከሰነዱ ብቻ ግልጽ ካልሆነ፣ የኪሣራውን ባህሪ የሚገልጽ የሰነድ አጭር ማብራሪያ/መግለጫ፣ እና (4) በስምምነቱ ላይ የተሳተፈ የቡድኑ አባል ለደረሰበት ኪሳራ ከሌላ ምንጭ ካሳ እንዳልተከፈለው የሚያረጋግጥ መግለጫ። የይገባኛል ጥያቄውን የሚደግፉ ሰነዶችም ደረሰኞችን ወይም ሌሎች የወጡ ወጪዎችን መዝግበው የያዙ በይገባኛል ጥያቄ አቅራቢው "በራሱ ያልተዘጋጁ" ሰነዶችን ሊያካትት ይችላል። እንደ በእጅ የተፃፉ ደረሰኞች ያሉ "በራስ የተዘጋጁ" ሰነዶች፣ በራሳቸው፣ ተመላሽ ገንዘብን ለመቀበል ሊቀርቡ የሚችሉ በቂ ማስረጃዎች አይደሉም፣ ነገርግን ሌሎች የቀረቡ ሰነዶችን ግልፅነት ለመጨመር ወይም ለመደገፍ እንደቀረቡ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

- **በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ የገንዘብ ማካካሻ:** የእልባት መስጫ ስምምነቱ ቡድን አባላት እስከ አራት(4) ሰዓታት ድረስ፣ ለሚደርሱ በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ በሰዓት ሀያ አምስት ዶላር እና ዜሮ ሳንቲም ($25.00)፣ ማካካሻ የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ ብቁ ናቸው። የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ ተሳታፊ አባላት ለውሂብ ጥሰቱ ምላሽ ለመስጠት የተወሰዱ እርምጃዎችን እና እያንዳንዱ እርምጃ የወሰደውን ጊዜ የሚያሳይ አጭር መግለጫ በማቅረብ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ ተመላሽ ማካካሻ ገንዘብ ማግኘት ይችላሉ። በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ የገንዘብ ማካካሻ ይገባኛል ጥያቄ ከፍተኛው የክፍያ ጣሪያ በአንድ ግለሰብ አንድ መቶ ዶላር እና ዜሮ ሳንቲም($100.00) ነው።

- **አማራጭ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ:** ከኪስ ውጪ በተደረገ ገንዘብ ሣቢያ ለሚደርሱ ኪሣራዎች ተመላሽ ወይም በይፋ ለተረጋገጠ የባከነ ጊዜ የማካካሻ ይገባኛል ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ ተሳታፊ የስምምነቱ ቡድን አባላት አማራጭ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ ለማግኘት የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። አንድ ተሳታፊ የስምምነት ቡድኑ አባል አማራጭ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ ይገባኛል ጥያቄውን ለመደገፍ ማንኛውንም ሰነድ ወይም ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ አይጠበቅበትም። ነገርግን፣ የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅፁ በዚህ የክፍያ ስምምነት መሠረት የሚቀርቡ ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ከመጠየቅ ይልቅ አማራጭ የጥሬ ገንዘብ ክፍያውን መጠየቅ እንደሚመርጥ በግልጽ ማሳየት አለበት። የሚሰጠው የገንዘብ ማካካሻ መጠን የሚጨምረው ወይም የሚቀነሰው ለእያንዳንዱ ሰው ድርሻ ተመጣጣኝ የሆነ ልክን መሰረት በማድረግ በቀረቡት ትክክለኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ብዛት እና ለእነዚህ ክፍያዎች በተያዘ በጀት/ፈንድ መጠን ላይ በመመርኮዝ ነው።

## 9. የቡድኑ አካል ሆኜ መቆየቴ ምን ያሳጣኛል?

የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባል ከሆኑ እና እራስዎን ከስምምነቱ ካላገለሉ፣ በዚህ እልባት መስጫ ስምምነት መፍትሔ ያገኙ የይገባኛል ጥያቄዎችን በተመለከተ በ SHA ወይም በስምምነቱ ከክስ ነፃ በወጡ ሌሎች ወገኖች ላይ ክስ የመመስረት፣ ክስ የማስቀጠል መብትዎን ወይም በማንኛውም ሌላ ክስ ላይ የመሳተፍ መብትዎን ያጣሉ። የእልባት መስጫ ስምምነቱ እርስዎ በዚህ ቡድን ውስጥ ከቆዩ የሚያጡትን ሕጋዊ የይገባኛል ጥያቄዎች ይገልጻል። ሙሉ የስምምነቱን ይዘት በሚከተለው የድረ ገፅ አድራሻ ላይ መመልከት ይችላሉ www.SeattleHADataIncident.com.

# ጥቅማጥቅሞችን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል—የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ማስገባት

## 10. ክፍያ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ከዚህ እልባት መስጫ ስምምነት ማንኛውንም ጥቅማጥቅም ለማግኘት የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ መሙላት እና ማስገባት አለብዎት። የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ በመስመር ላይ በድረ ገፅ አድራሻ www.SeattleHADataIncident.com መላክ ወይም በይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ባለው አድራሻ በፖስታ መላክ ይቻላል። የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ መመሪያዎችን በጥንቃቄ ማንበብዎን እርግጠኛ ይሁኑ፣ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ያካትቱ እና ፊርማዎን ያክሉ።

የእልባት መስጫ ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው የክፍያ ይገባኛል ጥያቄዎን ትክክለኛነት እና መጠን ለመወሰን ያቀረቡትን የይገባኛል ጥያቄን ይገመግማል።

ይህ ዝግ ቡድን ነው። ጥቅማጥቅሞቹ የሚገኙት ልዩ መለያ የተሰጣቸው የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባላት ብቻ ናቸው። የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባል ያልሆኑ ወይም ልዩ መለያ የሌላቸው ግለሰቦች የሚያቀርቧቸው ይገባኛል ጥያቄዎች በሙሉ ውድቅ ይሆናሉ። እርስዎም የእልባት መስጫ ስምምነቱ ቡድን አባል መሆንዎን የሚያምኑ ከሆነ እና ልዩ መለያ ከሌለዎት በስልክ ቍጥር 1-844-405-6502 ላይ ለስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው በመደወል የስምምነት ቡድኑ አባል መሆንዎን እና አለመሆንዎን በማረጋገጥ ልዩ መለያዎን ማግኘት ይችላሉ።

## 11. የማገኘው የክፍያ መጠን ምን ያህል ነው?

የሚያገኙት የክፍያ መጠን የሚወሰነው የይገባኛል ጥያቄ ካቀረቡበት የክፍያ መጠን ላይ የተፈቀደልዎ መጠንን እና በሁሉም የጸደቁ የይገባኛል ጥያቄዎች ጠቅላላ ክፍያ ላይ በመመርኮዝ ነው። የእልባት መስጫ ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው በይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጹ ላይ የቀረበው መረጃ የተሟላ እና ትክክለኛ መሆኑን ይወስናል። የእላባት መስጫ ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው ከማንኛውም አመልካች ተጨማሪ መረጃ ሊጠይቅ ይችላል። የእልባት መስጫ ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው ተጨማሪ መረጃ ከእርስዎ የሚጠይቅ ከሆነ እና በወቅቱ ካላቀረቡ፣ የክፍያ ይገባኛል ጥያቄዎ በስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪው ውሳኔ መሰረት ላይከፈልዎ ይችላል።

## 12. ክፍያዬን መቼ ነው የማገኘው?

ፍርድ ቤቱ የፍትሃዊነት ጉዳይን የሚመለከትበት የመጨረሻው ችሎት ልክ በ **9:00 A.M. PT** እ.ኤ.አ **አርብ፣ዲሴምበር 5 ቀን 2025** የሚካሄድ ሲሆን፣ ስምምነቱን ለማፅደቅ ወይም ላለማፅደቅ የሚወስን ይሆናል። ክፍያዎች የሚከናወኑት እልባት መስጫ ስምምነቱ ከፀደቀ እና ከተጠናቀቀ በኋላ ነው ( ማለትም ፍርድ ቤቱ ስምምነቱን አንዴ ካፀደቀው በኃላ በውሳኔው ላይ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም)። ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ጋር የተያያዙ ወቅታዊ መረጃዎች በሚከተለው የእልባት መስጫ ስምምነቱ ድረ-ገጽ አድራሻ ላይ የሚለጠፍ ይሆናል , www.SeattleHADataIncident.com. የክፍያው የሚከናወንበትን ጊዜ በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት በኢሜይል አድራሻ info@SeattleHADataIncident.com ላይ መልዕክት በመላክ የስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪውን ማነጋገር ይችላሉ።

# እርስዎን የሚወክሉ ጠበቆች

## 13. በዚህ ጉዳይ ጥብቅና የሚቆምልኝ አለ?

አዎን፣ Tousley Brain Stephens PLLC የሕግ ኩባንያ የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑን የሚወክል ይሆናል። የቡድኑ የህግ አማካሪ በመባል ይጠራሉ። ለሚሰጡት አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ አይጠየቁም።

## 14. የእራሴን ጠበቃ መያዝ እችላለሁ?

የራስዎን ጠበቃ መያዝ የሚፈልጉ ከሆነ ጠበቃ መቅጠር ይችላሉ፣ ነገር ግን ለዚህ ጠበቃ አገልግሎት ክፍያ የሚከፍሉት እራስዎ ይሆናሉ። ለምሳሌ፣ ከቡድኑ አማካሪ ውጪ ሌላ ሰው በችሎቱ ጉዳይዎን እንዲያስረዳ ከፈለጉ ጠበቃዎ እርስዎን ወክሎ ፍርድ ቤት እንዲቀርብል መጠየቅ ይችላሉ። በተጨማሪም ያለ ጠበቃ እርስዎ እራስዎ በችሎቱ መገኘት ይችላሉ።

## 15. ለጠበቃው ክፍያ የሚከፈለው እንዴት ነው?

ቡድኑን የሚወክሉ የሕግ አማካሪዎች እስካሁን ድረስ ለሰጡት የሕግ ነክ አገልግሎቶች ምንም ዓይነት ክፍያ አልተከፈላቸውም ወይም ለከፈሏቸው ክፍያዎች ወይም ከኪሳቸው ላወጡት ገንዘብ ተመላሽ አልተደረገላቸውም። ቡድኑን የሚወክሉ የሕግ አማካሪዎች ላበረከቱት የህግ አገልግሎት ክፍያ ከስምምነቱ ፈንድ/በጀት እንዲከፈል ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ አቅደዋል፣ ይህም ከተያዘው የስምምነት ፈንድ/በጀት ሠላሳ( 30%) ወይም $145,800 አይበልጥም። በቡድኑ የህግ አማካሪ ስር ያሉ ሁለቱ( 2) ጠበቆች እያንዳንዳቸው አራት ሺህ ዶላር እና ዜሮ ሳንቲም($4,000.00) የሚሆን የህግ አገልግሎት ክፍያ ይፈልጋሉ።

ፍርድ ቤቱ የቡድኑ የህግ አማካሪ የጠየቀውን የክፍያ እና የወጪ መጠን እንዲሁም ለቡድኑ ጠበቆች አንዲከፈል የቀረበውን የህግ አገልግሎት ክፍያን ማጽደቅ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ይወስናል። የቡድኑ ጠበቃ የክፍያ፣ የወጪ እና የህግ አገልግሎት ክፍያዎችን ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርበው **እ.ኤ.አ እስከ ኦክቶበር 6 ቀን 2025** ድረስ ብቻ ነው። ማመልከቻው www.SeattleHADataIncident.comበተሰኘ የስምምነቱ ድረ ገፅ ላይ ይገኛል፣ ወይም የእልባት መስጫ ስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪውን በማነጋገር የማመልከቻወን ኮፒ መጠየቅ ይችላሉ።.

## ከእልባት መስጫ ስምምነቱ እራስዎን ማግለል

## 16. ከእልባት መስጫ ስምምነቱ እራሴን ማግለል የምችለው እንዴት ነው?

የእልባት መስጫ ስምምነቱ ቡድን አባል ከሆኑ እና ከዚህ ስምምነት ምንም ዓይነት ጥቅም የማይፈልጉ ከሆነ እንዲሁም በዚህ ክርክር ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ የሲያትል መኖሪያ ቤቶች ባለሥልጣንን በራስዎ የመክሰስ መብትን ማቆየት ከፈለጉ ከስምምነት ቡድኑ እራስዎን ለማግለል እርምጃዎችን መውሰድ አለብዎት። ይህ እራስዎን ከስምምነት ቡድኑ ማስወጣት—ወይም "እራስዎን ማግለል" —ይባላል።

እ.ኤ.አ እስከ **ኦክቶበር 20 ቀን 2025**ድረስ ብቻ እራስዎን ከስምምነት ቡድኑ ማግለል ይቻላሉ።. ለመውጣት ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ደብዳቤ ወይም ፖስት ካርድ በU.S. mail መላክ አለብዎት። በደብዳቤዎ ወይም በፖስት ካርድዎ ላይ የሚከተሉትን ማካተት አለብዎት:-

- የክስ ጉዳዩን መጠሪያ ስም፣ *Lewis et al. v. Seattle Housing Authority*, የጉዳይ ቁጥር. 24-2-16171-6-SEA (የዋሽንግተን ግዛት ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ኪንግ ካውንቲ)፣ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ቅርብ የጉዳዩ መጠሪያ ስም፤;
- ሙሉ ስምዎን፣ ወቅታዊ መገኛ አድራሻዎን፣ እና የእራስዎን ፊርማ፤
- በሰነዱ አናት ላይ" የመገለል ጥያቄ ስለማቅረብ " የሚል ቃል ወይም ከእልባት መስጫ ስምምነቱ መውጣት እንደሚፈልጉ የሚያሳይ መግለጫ

ለመገለል የሚያቀርቡትን ጥያቄ በፖስታ መላክ ያለብዎት እ.ኤ.አ እስከ **ኦክቶበር 20 ቀን, 2025** ድረስ ብቻ ሲሆን የመላኪያ አድራሻ ለ:-

SHA Data Settlement
P. O. Box 1068
Baton Rouge, LA 70821

ተፈላጊ የሆነውን መረጃ ማካተት ካልቻሉ የይገባኛል ጥያቄዎ የተሳሳተ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን የስምምነት ቡድኑ አባል ሆነው ይቆያሉ እንዲሁም ስምምነቱን ለመቀበል ሕጋዊ ግዴታ ይኖርብዎታል በተጨማሪም በስምምነቱ መፍተሔ የሚሰጠው ጉዳይን መቃወም አይችሉም።

## 17. የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ አባል ከሆንኩ እና እራሴን ከቡድኑ ካላገለልኩ በቀጣይ በዚሁ ጉዳይ ላይ ተከሳሽ ላይ ክስ መመስረት እችላለሁን?

እራስዎን ከስምምነቱ ካላገለሉ በስተቀር፣ በዚህ ስምምነት መፍትሔ በሚያገኙ ጉዳዮች ላይ ተከሳሹን የመክሰስ መብት አይኖርዎትም።

## 18. እራሴን ካገለልኩ ምን ይፈጠራል?

እራስዎን ከእልባት መስጫ ስምምነቱ ካገለሉ የስምምነቱ ብድን አባላት የሚያገኙት ዓይነት ሙብት አይኖርዎትም። የእልባት መስጫ ስምምነቱ አካል በመሆን ምንም ዓይነት ክፍያ ወይም ጥቅማጥቅም አያገኙም። በእልባት መስጫ ስምምነቱ፣ መፍትሔ ያገኙ ጉዳዮች ወይም ሌሎች ትዕዛዞች ወይም የፍርድ ውሳኔዎች በእርስዎ ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም። በክርክሩ ላይ የተነሱ የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ በራስዎ ወጪ በተናጠል ክስ የመመስረት ሙብትዎ ይጠበቃል።

በተጨማሪም፣ ከእልባት መስጫ ስምምነቱ እራስዎን ካገለሉ፣ ስምምነቱ በእራስዎ ላይ ተፅዕኖ ስለማያሳድር ከዚህ ስምምነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተቃውሞ ማቅረብ አይችሉም። በእልባት መስጫ ስምምነቱ ላይ ተቃውሞ ካቀረቡ እና እራስዎን ለማግለል ከጠየቁ ተቃውሞዎ ተቀባይነት አይኖረውም እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ከስምምነቱ ለመውጣት እንደመረጡ አደርጎ ይቆጠራል።

# በእልባት መስጫ ስምምነቱ ላይ አስተያየት መስጠት ወይም መቃወም

## 19. እልባት መስጫ ስምምነቱን ካልወደድኩት ለፍርድ ቤቱ እንዴት ማስረዳት እቻላለሁ?

የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድን አባል ከሆኑ እና ከስምምነቱ እራስዎን ካላገለሉ ሙሉ ስምምነቱን ወይም ከፊል የስምምነቱን ክፍል ካልወደዱት ወይም ካልተስማሙ ስምምነቱን መቃወም ይችላሉ። ፍርድ ቤቱ የእልባት መስጫ ስምምነቱን ማጽደቅ የለበትም ብለው የሚያስቡበትን ምክንያት ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ። ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ከማስተላለፉ በፊት የእርስዎን አመለካከት ከግምት ውስጥ ያስገባል።

**<u>የሚቀርቡ ተቃውሞዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው</u>**: (i) የፍርድ ሂደቱን መጠሪያ ስያሜ፤ (ii) የስምምነት ቡድኑ አባል ሙሉ ስም፣ የፖስታ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤ (iii) ተቃውሞው የቀረበበትን ልዩ ምክንያቶች እንዲሁም ተቃውሞውን የሚደግፉ ማናቸውንም ሕጋዊ መሠረቶች እንዲሁም ሰነዶችን የያዘ የጽሑፍ መግለጫ፤ (iv) ተቃውሞዎ በተናጠል ተቃውሞ ያቀረበውን ግለሰብ፣ የተወሰኑ የቡድኑን አባላት፣ ወይም ሙሉ ቡድኑን የሚመለከት መሆን አለመሆኑን በግልጽ በፅሑፍ ማብራራት ይኖርብዎታል። (v)ተቃውሞ አቅራቢውን የሚወክሉ ማንኛውም ጠበቆች ማንነት፤ (vi) የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ አባል( ወይም ጠበቃው/ዋ) በመጨረሻው የውሳኔ ማፅደቂያ ችሎት ላይ የመገኘት ፍላጐት እንዳለው የሚገልጽ መግለጫ፤ እና( vii) የእልባት መስጫ ስምምነት ቡድኑ አባል ፊርማ።

ተቀባይነት ያለው ሆኖ ለመገኘት፤ አግባብ ባለው ቅጽ ላይ የተፃፈ የተቃውሞ ማሳወቂያ የፖስታ ምልክት (postmark) ቀን በማካተት እ.ኤ.አ እስከ**አክቶበር 20 ቀን 2025**ድረስ ብቻ ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ ሊላክ ይገባል።

SHA Data Settlement
P. O. Box 1068
Baton Rouge, LA 70821

በእልባት መስጫ ስምምነቱ ላይ ተቃውሞ ለማቅረብ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ማንኛውም የስምምነት ቡድን አባል በተናጠል ክስ ለመመስረት እና/ወይም በስምምነቱ ላይ ተቃውሞ ለማቅረብ ሊኖረው የሚችለውን ማንኛውንም እና ሁሉንም ሙብቶች ያጣል እንዲሁም በስምምነቱ እና በክሱ ውስጥ ባሉ ሁሉም የፍርድ ሂደቶች፣ ትዕዛዞች እና የፍርድ ውሳኔዎች ሁሉ ተገዢ ይሆናል። የእልባት መስጫ ስምምነቱን ለመቃወም የሚያስችለው ብቸኛው መንገድ በዚህ ሰነድ ውስጥ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አማካይነት ብቻ ይሆናል።

## 20. የእልባት መስጫ ስምምነቱን በመቃወምና ራሴን ከስምምነቱ በማግለል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መቃወም ማለት በእልባት መስጫ ስምምነቱ ውስጥ በተካተተ የሆነ ነገር አለመስማማትዎን መግለፅ ማለት ነው። በእልባት መስጫ ስምምነቱ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ የሚችሉት የስምምነቱ ቡድን አባል ከሆኑ እና ከስምምነቱ እራስዎን ካላገለሉ ብቻ ነው። እራስዎን ማግለል ማለት በዚህ ስምምነት ውስጥ የቡድኑ አካል መሆን እንደማይፈልጉ ለፍርድ ቤቱ መግለፅ ማለት ነው። ከእልባት መስጫ ስምምነቱ እራስዎን ካገለሉ ስምምነቱ ከእንግዲህ እርስዎን ስለማይመለከተዎ ለመቃወም ወይም የይገባኛል ጥያቄ ቅጽ ለማቅረብ ምንም መሠረት አይኖርዎትም።

## ፍርድ ቤቱ የፍትሃዊነት ጉዳይን የሚመለከትበት የመጨረሻ ችሎት

### 21. ፍርድ ቤቱ እልባት መስጫ ስምምነቱን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የሚወስነው መቼ እና የት ነው?

ፍርድ ቤቱ የፍትሃዊነት ጉዳይን የሚመለከትበት የመጨረሻ ችሎት ልክ በ **9:00 A.M. PT** እ.ኤ.አ **አርብ, ዲሴምበር 5 ቀን 2025** , በ King County Superior Courthouse, በቦታው 516 3rd Ave, Room C-203, Seattle, WA 98104 የሚያካሄድ ይሆናል. በችሎቱ ወቅት ፍርድ ቤቱ፣ የቀረበው እልባት መስጫ ስምምነት ፍትሃዊ፣ ምክንያታዊና በቂ መሆን አለመሆኑን ይመረምራል። ፍርድ ቤቱ የቡድኑ ህግ አማካሪዎች ይከፈሉን ሲሉ የሚቀርቧቸው የጥብቅና ክፍያዎች፣ ወጪዎች እና ክፍያዎችን እንዲሁም የቡድኑ ህግ አማካሪዎች የአገልግሎት ክፍያዎችን ማጽደቅ ወይም አለማፅደቅን በተመለከተ ሊመረምር ይችላል። ተቃውሞዎች ካሉ ፍርድ ቤቱ ይህን ከግምት ያስገባል። ፍርድ ቤቱ በችሎቱ ላይ ለመናገር የጠየቁ ሰዎችን ለመስማት ሊመርጥ ይችላል። በችሎቱ ላይ ወይም ከችሎቱ በኋላ ፍርድ ቤቱ እልባት መስጫ ስምምነቱን ለማጽደቅ ወይም ላለማፅደቅ ይወስናል። ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሚሳውቅበት የጊዜ ገደብ ምን ያህል እንደሆነ አልተቀመጠም።

### 22. የፍትሃዊነት ጉዳይ መመልከቻ የመጨረሻ ችሎት ላይ መገኘት አለብኝ?

የለብዎትም. የቡድኑ ህግ አማካሪ ጠበቃ ፍርድ ቤቱ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ይሰጣል። ሆኖም፣ በራስዎ ወጪ ፍርድ ቤቱ የፍትሃዊነት ጉዳይን በሚመለከትበት የመጨረሻ ችሎት ላይ መገኘት ይቻላሉ። ተቃውሞ ካቀረቡ፣ ስለ ጉዳዩ ለማስረዳት ወደ ፍርድ ቤት መምጣት አይጠበቅብዎትም። በተጨማሪም፣ በራስዎ ወጪ የራስዎን ጠበቃ መቅጠር ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህን ማድረግ አይጠበቅብዎትም።

### 23. በችሎቱ ላይ መናገር ይፈቀድልኛል?

የፍትሃዊነት ጉዳይ በሚታይበት የመጨረሻው ችሎት ላይ ለመናገር ፍርድ ቤቱን ፍቃድ መጠየቅ ይችላሉ። ይህን ለማድረግ ከላይ በጥያቄ ቁጥር 19 ላይ የተሰጡ መመሪያዎች መከተል አለብዎት። እራስዎን ከስምምነቱ ካገለሉ በችሎቱ ላይ መናገር አይችሉም።

## ምንም እርምጃ ካልወሰዱ

### 24. ምንም እርምጃ ካልወሰዱ ምን ይፈጠራል?

ምንም እርምጃ ካልወሰዱ ከዚህ እልባት መስጫ ስምምነት የሚገኝ ክፍያ አይቀበሉም ወይም ለመቀበል ብቁ አይሆኑም። ፍርድ ቤቱ ስምምነቱን ካፀደቀ እና እርስዎ ምንም እርምጃ ካልወሰዱ ለስምምነቱ ውሎች ተገዢ ይሆናሉ። ይህም ማለት በሲያትል የመኖሪያ ቤቶች ባለስልጣን ላይ ወይም በስምምነቱ ነፃ የወጡ ግለሰቦች ላይ በዚህ ክስ ውስጥ የተካተቱ ፣ በስምምነቱ የተፈቱ፣ እና በስምምነቱ የተጠናቀቁ ጉዳዮችን በማንሳት አዲስ ክስ መጀመር፣ ነባሩን ክስ ማስቀጠል ወይም የማንኛውም ሌላ ክስ አካል መሆን አይችሉም።

## የበለጠ መረጃ ስለማግኘት

### 25. ስለ ስምምነቱ ተጨማሪ ዝርዝሮች ማግኘት ይቻላል?

አዎን፣ ይህ ማስታወቂያ ስምምነት ላይ የተደረሰበትን ሃሳብ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። ተጨማሪ ዝርዝሮች በስምምነቱ ውሎች እና ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች ሰነዶች ላይ በሚከተለው ድረገፅ አድራሻ ማግኘት ይችላሉ www.SeattleHADataIncident.com.

### 26. ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

የእልባት መስጫ ስምምነቱን ድረ ገፅ በ www.SeattleHADataIncident.com,ላይ ይጎብኙ በዚህ ድረ ገፅ ላይ የክፍያ ይገባኛል መጠየቂያ ቅጽ፣ የእልባት መስጫ ስምምነት ውሎቹን ቅጂ፣ ስለ ስምምነቱ ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች እንዲሁም ለክፍያ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን የሚረዱ መረጃዎችን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችንም ያገኛሉ።

የስምምነት ጉዳይ አስተዳዳሪውን በነፃ የስልክ ጥሪ መስመር ቁጥር 1-844-405-6502ላይ በመደወል ወይም በሚከተለው አድራሻ ደብዳቤ በመላክ ያነጋግሩ።

SHA Data Settlement
P.O. Box 1068
Baton Rouge, LA 70821

**እባክዎን ስለዚህ እልባት መስጫ ስምምነት ወይም ስለ ክሱ ሂደት ለመጠየቅ ፍርድ ቤቱን፣ የፍርድ ቤት አስተዳደር ጽሕፈት ቤቱን ወይም ተከሳሹን ለማግኘት አይሞክሩ።**